የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፻፪
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33th Year No.102
Addis Ababa 17, April 2025

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፺፪/፪ሺ፲፯
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዳሪ ትምህርት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ
ገጽ ………………………………….፫ሺ፱፻፸፯

CONTENT

REGULATION No. 192/2025
ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE BOARDING SCHOOL
Page…………………………………………………………3977

## ደንብ ቁጥር ፻፺፪/፪ሺ፲፯

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዳሪ ትምህርት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመማር ላይ ከሚገኙት ወጣት ተማሪዎች መካከል የላቀ ውጤት ያላቸውን በመለየትና ወደ አዳሪ ትምህርት ቤት በማስገባት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በክህሎታቸውና በእውቀታቸው የላቁ ተማሪዎችን በማፍራት ለሌሎች ተማሪዎች አርዓያ በመሆን በተማሪዎች መካከል የመነሳሳትና የውድድር መንፈስ እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የላቀ ውጤት ኖሯቸው ነገር ግን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ምክንያት ተገቢውን ድጋፍ የማያገኙትን በማገዝ እና ለትምህርት ጥራት መሻሻል የአዳሪ ትምህርት ቤቶችን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ እና

## REGULATION No. 192/2025

## ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE BOARDING SCHOOL

**WHEREAS**, it has become necessary to establish a spirit of inspiration and competition among students by identifying those who excel in attending high schools in Addis Ababa and entering boarding school, providing proper supervision and support to other students who excel in their skills and knowledge, as a model for students;

**WHEREAS**, it is found necessary to establish boarding schools for the improvement of the quality of education and with the help of those who live to excel but do not receive proper support due to socio-economic hardship; and

የዐይነ-ስውራን ልዩ የትምህርት ፍላጎቶችን ለማሟላት እና ሀገሪቱ የአካል ጉዳተኞች መብቶችን ለማክበር ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን እና ፍትሃዊ የትምህርት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ግብዓቶችን፣ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን እና ተገቢ ሥርዓተ ትምህርት ያላቸው ተቋማትን ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

ፈጣንና ከፍተኛ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች በማወዳደርና በአዳሪ ትምህርት ቤቱ በማስገባት ተገቢውን ትምህርት፣ ክህሎት፣ አገልግሎት እና ድጋፍ በመስጠት ማስተማር ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው፣ ለቤተሰባቸው ብሎም ለሃገራቸው ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ እና ሌሎችም ተማሪዎችና ትምህርት ቤቶች በአዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውጤት ተነሳስተው በያሉበት ውጤታቸውንና የትምህርት ቤት ደረጃቸው ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው በመሆኑ፤

ውጤታማ ተማሪዎች እና በቂ የትምህርት እድሎችን በማመቻቸት ለአዳሪ ትምህርት ቤቱ እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ህይወት ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እና አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ አንቀፅ ፺፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዳሪ ትምህርት ቤት ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፺፪/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

**WHEREAS**, it has become necessary to establish necessary resources, skilled professionals, and institutions with appropriate curricula to meet the special educational needs of blind people and ensure the international agreements and equitable access to education that the country has ratified to respect the rights of people with disabilities;

**WHEREAS**, it is necessary to other students and schools are motivated by the results of boarding school students, as they are highly instrumental in improving their grades and school levels and comparing fast, high-achieving students and entering the boarding school, teaching them with proper education, skills, services and support, students are able to be self-sufficient, to do effective work for their families and for their country;

**WHEREAS**, it has become necessary to contribute fully to social, economic and cultural life by facilitating effective students and adequate educational opportunities since it is important for the boarding school as well as at the national level;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 93 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Addis Ababa City Government Land Tenure Registration and Information Agency has issued this Regulation.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as:"Addis Ababa City Government Regulation to Provide for the Establishment of the Boarding School Regulation No.192/2025".

### 2. Definition

Unless the context or the phrase otherwise requires in this Regulation:

1. "**City**" means the Addis Ababa City;
2. "Region" means any state incorporated under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, which includes the Administrations of Addis Ababa and Dire Dawa City;

፫. **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፬. **"ከንቲባ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ነው፤

፭. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ቢሮ ነው፤

፮. **"ተማሪ"** ማለት በብርሃን የዐይነ-ስውራን፣ በእቴጌ መነን ልጃገረዶች እና ገላን ወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤቶች በመደበኛ ተማሪነት ተመዝግቦ ትምህርቱን በመከታተል ላይ የሚገኝ ተማሪ ነው፤

፯. **"ዐይነ-ስውር"** ማለት የዐይን ብርሃን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያጣ እና ትምህርትን በቀለም የተፃፈውን ሳይሆን በማዳመጥ እና በመዳሰስ የሚማር ሰው ነው፤

፰. **"ትምህርት ቤት"** ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመው ብርሃን የዐይነ-ስውራን፣ እቴጌ መነን ልጃገረዶች እና ገላን ወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤቶች ናቸው፤

፱. **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት ትምህርት ቤቱን በበላይነት የሚመራ ኃላፊ ነው፤

፲. **"ምክትል ዋና ዳይሬክተር"** ማለት በትምህርት ቤቱ ውስጥ በተለያዩ ሥራ ዘርፎች ላይ የሚሰየሙ በምክትል ዋና ዳይሬክተርነት የሚመሩ ናቸው፤

፲፩. **"ትምህርት አመራር"** ማለት ርዕሰ መምህር፣ ምክትል ርዕሰ መምህራን እና ሌሎች በአመራርነት የሚሰሩ መምህራን ነው፤

፲፪. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም የህግ የሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

፫. <u>**የፆታ አገላለጽ**</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. "**Region**" means any state incorporated under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, which includes the Administrations of Addis Ababa and Dire Dawa City;
4. ''**Mayor**" means mayor of Addis Ababa city government;
5. "**Bureau**" means the Education Bureau of the City Government of Addis Ababa;
6. "**Student**" means a student who is enrolled as a regular student in the boarding schools of the Brehan blinds, Empress Menen Girls and Galan boys and is attending school;
7. "**Blind**" means a person who has lost all or part of the light of the eye and learns learning by listening and exploring, rather than what is written in colour;
8. "**School**" means boarding schools of blind, Empress Menen Girls and Galan Boys that are established under this regulation;
9. "**Director General**" means Head who leads the school;
10. "**Deputy Director General**" means those who are appointed to different areas of work in the school, headed by a Deputy Director General;
11. "**Education Leadership**" means principal, vice principals and other teachers working as leadership;
12. "**Person**" means any natural or juridical person.

3. <u>**Gender Expression**</u>

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine gender.

**፬. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በብርሃን የዐይነ-ስውራን፣ በእቴጌ መነን ልጃገረዶች እና ገላን ወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የትምህርት ቤቱ መቋቋም፣ አገልግሎት፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር</u>**

**፭. <u>መቋቋም</u>**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብርሃን የዐይነ-ስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት (ከዚህ በኋላ “ትምርት ቤት” ተብሎ የሚጠራ) እራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እቴጌ መነን ልጃገረዶች ትምህርት ቤት (ከዚህ በኋላ “ትምርት ቤት” ተብሎ የሚጠራ) እራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፫. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገላን ወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤት (ከዚህ በኋላ “ትምርት ቤት” ተብሎ የሚጠራ) እራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፬. የትምህርት ቤቱ ተጠሪነት ለትምህርት ቢሮው ይሆናል፡፡

**፮. <u>አርማ</u>**

ትምህርት ቤቱ የራሱ አርማ ይኖረዋል፡፡

**፯. <u>ዓላማ</u>**

ትምህርት ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. ተማሪዎችን በሥነ-ምግባር፣ በትምህርት፣ በክህሎት፣ በቡድን የመስራት ችሎታቸውን ማጠናከር እና ለሌሎች አርዓያ እንዲሆኑ ማስቻል፤

፪. ተማሪዎች ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ግላዊ ማንነታቸው እንዲጎለብት ልምድና እድሎችን መስጠት፤

4. **<u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall be applicable for the Boarding Schools of Brehan blinds, Empress Menen Girls and Galan boys.

**<u>PART TWO</u>**

**<u>ESTABLISHMENT, SERVICE, ORGANIZATION, POWERS AND DUTY</u>**

5. **<u>Establishment</u>**

1. The Addis Ababa city government Brehan Blind Boarding School (hereafter referred to as “**School**”) was established under this Regulation as the Executive Branch of the City Government with an independent legal personality;

2. The Addis Ababa City Government Empress Menen Girls' School (hereafter called “**School**”) was established under this Regulation as the Executive Branch of the City Government with an independent legal personality;

3. The Addis Ababa City Government Galan Boys Boarding School (hereafter called “**School**”) was established under this Regulation as the Executive Branch of the City Government with an independent legal personality;

4. The Schools are accountable for the Education Bureau.

6. **<u>Logo</u>**

The School will have its own logo.

7. **<u>Objective</u>**

The School will have the following Objectives:

1. Enforcing students with ethics, education, skills, ability to work in groups, and to be role models for others;

2. Providing students with experience and opportunities to develop their cultural, social, and personal identity;

፫. ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸውን የሚመሩበትን ክህሎት እንዲያዳብሩ በማድረግ እድሎችን ለማቻቸት፤

፬. ትምህርት ቤቶቹ በሳይንስና በቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል እንዲሆኑ፣ በጥናትና ምርምር ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፤

፭. የትምህርት ቤቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል ተቋማዊ አሰራር መዘርጋት እና እሴትን ማጠናከር፤

፮. በአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ ተጠያቂነትን ማስፈን፤

፯. የትምህርት ሴክተሩን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት በሚያስችል መልክ የተቀመጡ እሴቶችን በአዳሪ ትምህርት ቤቶቹ በማስረፅ ለውጤታማ ሥራ የተዘጋጀ አመራር፣ መምህር፣ ባለሙያ፣ ሠራተኛ እና ተማሪ መፍጠር፡፡

## ፰. <u>የትምህርት ቤቱ አደረጃጀት</u>

የትምህርት ቤቱ አደረጃጀት፡-

፩. ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣

፪. አካዳሚክ ኮሚሽን እና

፫. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

## ፱. <u>የትምህርት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ትምህርት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በቅበላ መስፈርቱ መሰረት ተማሪዎች ስለመመልመላቸው ያረጋግጣል፣ ይቀበላል፤

፪. የተማሪዎችን ግለ ታሪክና መረጃ ይመዘግባል፣ በአግባቡ ያደራጃል፤

፫. ለተማሪዎች የመኝታ፣ የምግብ፣ የጤና እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፬. ጥራት ያለው እና ደረጃውን የጠበቀ የትምህርት አገልግሎት ይሰጣል፣ በየጊዜው የተማሪዎችን የዕውቀት እና ክህሎት ሽግግር ይከታተላል፤

3. To facilitate opportunities by allowing students to develop the skills to guide their future;

4. To make the schools a center of excellence in science and technology, to focus on research and research;

5. Developing an institutional system to achieve the school's goals and strengthening value;

6. Ensuring the participation of the parties concerned in administrative decision-making, establishing accountability;

7. Creating leadership, teacher, professional, worker, and student dedicated to effective work by instilling in its boarding schools the values set in such a way as to achieve the vision and mission of the educational sector.

## 8. <u>Organization of the school</u>

Organization of the School:

1. Executive Director and Deputy General Directors, respectively
2. Academic Commission and
3. Other important work units and workers it will have.

## 9. <u>Powers and Duty of the School</u>

The School will have the following powers and functions:

1. It ensures, accepts, that students are recruited according to the admissions criteria;

2. It records students' autobiographies and information, organises them appropriately;

3. It provides students with access to sleep, food, health, and other essential services;

4. It provides quality and standardised education services, regularly monitoring students' transfer of knowledge and skills;

፭. ለተማሪዎች የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና መፃህፍት በማሰባሰብ ቤተ መፃህፍት፣ ቤተሙከራ እና ወርክ ሾፖችን ያደራጃል፤

፮. የመምህራንና የትምህርት አመራሩን የማስፈፀም አቅም ለመገንባት የሚረዱ ሥራዎችን ይሰራል ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በቢሮው ሲፈቀድ በሌላ አካል እንዲሰራ ያደርጋል፤

፯. ተማሪዎች በቀጣይነት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ህብረተሰብ ውስጥ ተወዳዳሪና ብቁ እንዲሆኑ ያዘጋጃል፤

፰. የትምህርት ቤቱ ግቢ፣ መገልገያ ክፍሎች እና የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች ምቹ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፱. ልዩ የመማር ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ ይደግፋል፤

፲. መማር ማስተማሩ የተቀላጠፈና ውጤታማ እንዲሆን ተከታታይ ምዘና እና ፈተና ይሰጣል፤

፲፩. የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ያጠናክራል፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂዎች እና ሌሎች ተሞክሮዎችን ያስፋፋል፣ መምህራን እና ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

፲፪. የተማሪዎችን ተሰጥኦ በመለየት እንዲዳብር ያደርጋል፤ በበጎ ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

፲፫. የትምህርት ማስረጃ የምስክር ወረቀት ለተማሪዎች ይሰጣል፤

፲፬. ከፍተኛ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች እና አርዓያ ለሆኑ እና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ መምህራንና ሠራተኞች የዕውቅና ሽልማት ይሰጣል፤

፲፭. ተደራራቢ የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች የአካል ድጋፍ እና ለአካል ጉዳታቸው ድጋፍ አገልግሎት የሚውል ግብዓት እንዲሟላ ያደርጋል፤

፲፮. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፤

5. It organizes libraries, labs and Workshops, collecting educational resources and books for students to use;

6. It undertakes tasks to build the capacity of the faculty and educational leadership to carry out or to be done by another party when allowed by the office as needed;

7. It prepares students to continuously compete and qualify in higher educational institutions and society;

8. The School's compound, facilities rooms, and teaching-learning process make them ideal for students;

9. It uniquely supports students with special learning needs;

10. Learning provides a series of assessments and tests to ensure that teaching is efficient and effective;

11. It strengthens research and research activities, promotes science and technologies and other experiences, and encourages faculty and students to participate;

12. It identifies and develops students' talents and encourages them to engage in good works;

13. Certificate of educational evidence is offered to students;

14. It awards recognition to high-achieving students and teachers and staff who are role models and have made significant contributions;

15. It provides for the fulfilment of physical support for students with overlapping disabilities and resources for their disability support services;

16. It carries out other related activities required to achieve its purpose;

፲፯.የከተማ አስተዳደሩን የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀፅ ፲፮ መሰረት የተዘረዘሩ የወል ሥልጣኖች ይፈጽማል፡፡

፲. **የዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተር አመዳደብ**

ቢሮው የትምህርት ቤቱን ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሹመት ለከንቲባ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ይሾማል፡፡

፲፩. **የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ የተመለከቱትን የትምህርት ቤቱ ሥልጣንና ተግባርን በሥራ ላይ ያውላል፤

፪. የትምህርት ቤቱን የስትራቴጂክና መሪ ዕቅዶችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፫. በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባ እና ስንብት ለቢሮ አቅርቦ ያጸድቃል፤

፬. የትምህርት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በማጸደቅ በሥራ ላይ ያውላል፤

፭. ለትምህርት ቤቱ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

፮. የትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ ሊጋራው የሚችል ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶችን በመቅረጽ እንዲያውቁት ያደርጋል፤

፯. ከትምህርት ቤቱ መሪ እና ስትራቴጂክ ዕቅድ በመነሳት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እቅድ እንዲያወጡ ያደርጋል፣ ዕቅዱም ትምህርት ቤቱ ሊያሳካቸው ያሰባቸው ግቦች ላይ መመስረቱን ያረጋግጣል፤

፰. የተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሳደግና የትምህርት ጥራት ለማምጣት የሚያስችል ምቹ የመማሪያ እና የማስተማሪያ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፱. የመማር ማስተማር ሥራን በቅርበት በመከታተል ችግር በሚታይባቸው ጉዳዮች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

17. It exercises common powers enumerated under Article 16 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023.

10. **Assignment of Director-General and Deputy Director-General**

Bureau submits the appointment of Executive director and Deputy Executive director nomination to the Mayor; upon approval shall appoint thereof,

11. **Power and duties of the Director-General**

1. He takes into effect the power and duty of the school as indicated by Article 9 of this Regulation;
2. He develops the school's strategic and guiding plans, making them operational when approved;
3. He employs, administers personnel; employs officials responsible for it; provides for and approves allocations and dismissals to Bureau under the Civil Service Law;
4. He develops and approves the school's annual work program and budget and is in effect;
5. Funds will be spent under the budget and work program approved for the school;
6. He makes the school community aware of it by shaping vision, mission, and values that it can share;
7. Based on the leader and strategic plan of the school, it will lead the Deputy Directors General to make plans, and the plan will ensure that the school will be based on the goals it intends to achieve;
8. He creates a comfortable learning and instructional environment to enhance students' educational achievement and bring them quality of education;
9. He takes the necessary remedial action in cases where it is problematic to closely monitor the teaching of learning;

፲. ህብረተሰቡና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከትምህርት ቤቱ ጋር ጠንካራና የማያቋርጥ ግንኙነት እንዲኖር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፲፩.ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮችን እና በስሩ ለሚገኙ ዘርፎች የውጤት ተኮር እቅድ ያወርዳል፣ የምዘና ሂደቱም በወቅቱ እንዲከናወን ያደርጋል፤

፲፪.በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ ሥራ ለመገመገም እና የመፍትሄ ሀሳብ ለማስቀመጥ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እና ወላጅ ተማሪ መምህራን ህብረት የሚሳተፉበት መድረክ ያዘጋጃል፣ ሪፖርት ያደርጋል፤

፲፫.የዲሲፕሊን ጉድለቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ ከዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚቀርብለትን የውሳኔ ሀሳብ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ውጤቱንም ለሚመለከተው ያሳውቃል፤

፲፬.የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የውስጥ ክትትልና ድጋፍ ሂደቱን ይመራል፣ ይከታተላል፤ ይደግፋል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፤

፲፭.የትምህርት ቤቱን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለቢሮው በወቅቱ ያቀርባል፤

፲፮.ትምህርት ቤቱን ከሦስተኛ ወገን ጋር ለሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ለትምህርት ቢሮ በቅድሚያ በማሳወቅ ሲፈቀድለት ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፯.እንደአስፈላጊነቱ ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

፲፰.ልዩ ልዩ ክፍያዎችን በከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሰረት ተዘጋጅተው ሲቀርቡ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ይወስናል፤

፲፱.ቢሮው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፪. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፦

፩. የትምህርት ቤቱን የዘርፍ ተግባራት ያቅዳሉ፣ ያደራጃሉ፣ ያስተባብራሉ፤ ይመራሉ፤

10. He provides an environment for the community and Non-Governmental Organizations to maintain a strong and constant relationship with the school;
11. He brings down results-oriented planning for Deputy General Directors and sectors under it, and makes the assessment process take place in a timely manner;
12. The School Community and Parent Student Teachers Union organizes, reports, a forum in which to participate to review work and put forward a solution at the end of each quarter;
13. He will lead to corrective action against disciplinary flaws, will make a decision by examining a recommendation from the disciplinary committee; will monitor its implementation, and report the results to the one concerned;
14. He directs, monitors, supports, provides feedback on the process of internal monitoring and support for the teaching and learning process;
15. He would submit the School's job performance report to the Bureau on a timely basis;
16. He implements the school when it is authorized by first informing the Bureau of Education of its relationships with a third party;
17. He may delegate, as required, part of its power and duty to the School's superiors and staff;
18. He determines the various payments by ensuring their validity when they are made and presented under the City Government Finance Administration Law;
19. He performs other functions provided by the Bureau.

**12. <u>Power and Duty of Deputy Directors General</u>**

Deputy Directors-General will be accountable to the Director-General and will have the following power and duty:

1. They plan, organize, coordinate and guide the sectoral activities of the School;

፪. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናሉ፤

፫. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ ውክልና ሲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩን ወክለው ይሠራሉ፡፡

**፲፫. አካዳሚክ ኮሚሽን አባላት**

፩. የትምህርት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ................................................ ሰብሳቢ፤

፪. የትምህርት ቤቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ................................................ አባል፤

፫. የእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች ................................................ አባል፤

፬. ሁለት የተማሪዎች ተወካዮች አንድ ወንድ እና አንድ ሴት.............................................አባል፤

**፲፬. የአካዳሚ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት**

፩. የአካዳሚክ ኮሚሽኑን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ ሥራ ላይ ያውላል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፪. የሥርዓተ ትምህርትና የስልጠና ማሻሻያ ዕቅድ በማዘጋጀት ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፤

፫. የትምህርትና የተለየ ሥልጠና መርሀ ግብሮችን አዘጋጅቶ ለቢሮ በማቅረብ ያጸድቃል፣ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

፬. ተማሪዎችን የመማር ብቃት እድገት በየጊዜው እየፈተሸ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

፭. ከትምህርት ጋር የተያያዙ እውቅናና ሽልማቶች እንዲሰጡ ሃሳብ ያቀርባል፤

፮. በትምህርት ቤቱ ጥናትና ምርምሮች እንዲካሄዱ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎች እንዲበለጽጉ ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያስፈጽማል፣ ሂደቱንም ይገመግማል፤

፯. ምርጥ ተሞክሮ ይቀምራል፣ ያስፋፋል፤

፰. የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል፤

፱. ከዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

፲. አካዳሚክ ኮሚሽኑ በወር አንድ ጊዜ ጉባኤውን ያደርጋል፤ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም እንደአስፈላጊነቱ ጉባዔውን ሊያካሂድ ይችላል፡፡

2. They perform tasks that are given separately by the Director General;

3. In the absence of the Director-General, they act on behalf of the Director-General when delegated separately by the Director-General.

13. **Academic Commission Members**

1. The Executive Director of the School ............................................................Chairman

2. The School's Deputy Directors-General................................................ Member;

1. Each Department's Respondents......... Member;

2. Two Student Representatives, one Male and one Female..................................................Member

14. **Duty and Responsibility of the Academy Commission**

1. It prepares the plan of the Academic Commission, which when approved is at work, and pursues its implementation;

2. It provides for the Director-General with a plan for curriculum and training improvement;

3. It develops and approves the educational and specific training programs by submitting them to Bureau, ensuring that they are implemented;

4. The development of learning competence for students is constantly explored and orientated;

5. It proposes recognition and awards related to education;

6. It proposes that research be conducted at the school, that creative works of science and technology be enriched, enforces when approved, and evaluates the process;

7. It is picked best experience, expanded;

8. It sets up its own Internal Rule of the meeting procedure;

9. It carries out other duties from the Director-General;

10. The Academic Commission holds its conference once a month, in the event of an emergency; it may hold its conference as required.

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፭. በጀት**

የትምህርት ቤቱ የበጀት ምንጮች፡-

፩. ከከተማው አስተዳደር ከሚመደብ በጀት፤

፪. ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር በአይነትና በጥሬ ገንዘብ ከሚገኝ ዕርዳታና ስጦታ፤ እና

፫. ከሌላ ከማንኛውም ህጋዊ ምንጭ ይሆናል፡፡

**፲፮. ስለሂሳብ መዛግብት**

፩. ትምህርት ቤቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም እሱ በሚወክለው አካል ይመረመራል፡፡

**፲፯. የተማሪዎች ምልመላ እና ቅበላ**

፩. ተማሪዎች እንደአግባቡ በከተማው አስተዳደር ካሉ ትምህርት ቤቶች ወይም ከየክልሎች የሚመለመሉ ይሆናል፤

፪. የተማሪዎች የምልመላ እና የቅበላ ሥነ-ሥርዓት ቢሮው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር በሚያዘጋጀው መስፈርት መሰረት ይሆናል፡፡

**፲፰. የመምህራን ምልመላ**

የመምህራን ምልመላ እና ምደባን በተመለከተ ቢሮው በሚያወጣው ዝርዝር አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፲፱. የጥቅማ ጥቅም አሰጣጥ**

የጥቅማ ጥቅም ጥያቄዎችን በተመለከተ ቢሮው በሚያወጣው ዝርዝር አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፳. የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ**

የተማሪዎች ዲሲፕሊን ጉዳዮችን በሚመለከት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፩.ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የካቢኔው ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

15. **Budget**

The School's budget sources are:

1. From the budget allocated from the City Government;
2. From grants and gifts in kind and cash from the country and abroad; and
3. It will be from any other legal source.

16. **Accounting Records**

1. The School maintains a complete and accurate collection of accounting records;
2. Accounts and financial documents are examined by the Office of the Auditor General of the City Government or by the body it represents.

17. **Recruitment and Intake of Students**

1. Students may be recruited from Schools or from each region, such as those in the City Government, as appropriate;
2. The recruitment and admission procedure for students will be in accordance with the criteria that the Bureau sets in consultation with the relevant Authorities.

18. **Teacher Recruitment**

It applies in accordance with the Bureau's detailed implementation directive regarding teacher recruitment and placement.

19. **Benefit Giving**

It applies in accordance with the Bureau's detailed Execution Directive regarding benefit requests.

20. **Disciplinary Measurement Determination**

Students' discipline is determined by a Directive regarding matters.

21. **Inapplicable Laws**

Any regulation, directive or customary practice of the City Cabinet does not apply to issues covered by this Regulation.

፳፪. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ቢሮው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ሚያዝያ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡

**አዲስ አበባ ሚያዝያ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ ደሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

22. **<u>Power to Issue Directive</u>**

The Bureau may issue Directive to enforce this Regulation.

23. **<u>Effective Date</u>**

This regulation shall enter into force as of April 17, 2025.

**Done at Addis Ababa this 17 th day of April 2025.**

**Adanech Abiebie Desa**

**Mayor of Addis Ababa City**